# መመሪያ ቁጥር 1134/2018

# የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ ዝግጅት እና ስርጭት መመሪያ

ከጤና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያለዉ ማስታወቂያ በሚዘጋጅበት እና በሚሰራጭበት ወቅት ሙያዊ ስነ ምግባርን ባልተከተለ መልኩ መሆኑ በህብረተሰቡ ዉስጥ የተዛባ አመለካከት እንዲፈጠር እያደረገ በመሆኑ፤

የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ የሚያዘጋጁ እና የሚያስተላልፉ አካላት ሙያዊ ስነ-ምግባርን በተከተለ መልኩ እና የማህበረሰቡን ባህል የጠበቀ ሥራ ለመስራት የሚያስችላቸዉን ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና አገልግሎት ማስታወቂያዎች ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲመሩ ለማስቻል በጤና አገልግሎት አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 ላይ የእዚህ ስራ አዘገጃጀትና አሰረጫጨትን በተመለከተ የተመቀመጡ ግዴታዎችን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ በማስፈልጉ፤

የጤና ሚኒስቴር በጤና አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ “**የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ ቁጥር** 1134/2018” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ዉስጥ፤

1) “**አዋጅ**” ማለት የጤና አገልግሎት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር1362/2017 ነዉ፡፡
2) “**የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ**” ማለት ከጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የጤና ተቋም ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም ዓላማ እንዲተዋወቅ በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነዉ፤
3) “**አስነጋሪ**” ማለት የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ የሚነገርለት ወይም የሚተላለፍለት ሰዉ ነዉ፡፡
4) “**አስተተላላፊ**” ማለት በተለያየ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የህትመት ሽፋን ወይም ሌሎች መሰል መንገዶችን በመጠቀም የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ የሚያሰራጭ ሰው ነው፡፡
5) “**ማስራጫ መንገድ**” ማለት የጤና አገልግለት ማስታወቂያ ለማስተላለፍ የሚያገለግል የመገናኛ ብዙኃን፣ የዉጭ ማስታወቂያ፤የጤና ትምህርታዊ ዝግጅት፣ የቴሌኮሚኒኬሽን የፅሁፍና ድምፅ መልእክቶች ፣ የማህበራዊ ሚዲያና ድረ-ገፅ፣ የዲጂታል ሚዲያ ወይም ሌላ የማሰራጫ መንገድ ነዉ፡፡
6) “**መገናኛ ብዙሃን**” ማለት በመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 2(1) ላይ የተመለከተዉ ትርጓሜ ይኖረዋል፡፡
7) “**አግባብ ያለዉ አካል**” ማለት እንደ ቃሉ አገባብ የጤና ተቋማትን የሚቆጣጠር ተቋም ወይም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስጣን ማለት ነዉ፤
8) “**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

10) በአዋጁ ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ሌሎች ቃላትና ሀረጎች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ በሚያዘጋጅ፣ በሚያስነግር ወይም በሚያስተላልፈ ሰዉ ላይ በመላ ሀገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ አዘገጃጀት</u>

4. <u>ስለቋንቋ አጠቃቀም</u>

ማንኛውም የጤና አገልግሎት ይዘት ያለው ማስታወቂያ ሲዘጋጅ፡-

1) ታዳሚዉ ህብረተሰብ በሚናገረዉ ቋንቋ እና አገላለጽ፤
2) የአካል ጉዳተኞችን እና ልዩ ፍላጎት ያላቸዉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት እና አካታችነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ፤ እና
3) የማያሻማ ወይም የሙያ ቃላት ያልበዙበት፣

መሆን አለበት፡፡

5. <u>ይዘት</u>

1) የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ ሲዘጋጅ ይዘቱ፡-
   ሀ) የጤና ፖሊሲን ያከበረ፣ ሌሎች የጤና ጉዳዮችን ታሳቢ ያደረገ የማህበረሰቡን ጤንነት ወይም ደህንነት የጠበቀ መሆን አለበት፡፡
   ለ) መልዕክቱ የሚተላለፍለትን ታዳሚ ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡
   ሐ) የማህበረሰቡን ባህል እና እሴት የጠበቀ መሆን አለበት፣
   መ) እንደ "ተቀዳሚ ምርጫ" ፣ "የሁሉም ምርጫ" እና መሰል ገላጭ ቃላትን መጠቀም የለበትም፡፡
   ረ) የጤና ተቋሙ አገልግሎቱን ስለመሰጠቱ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
   ሰ) ጤና ተቋሙ በሚሰጠዉ አገልግሎት ምክንያት ያገኘዉ አገራዊ ወይም አለማቀፋዊ ሽልማት ካለ እና ስላገኘው ሽልማት ወይም እውቅና የሚያስተዋዉቅ ከሆነ ሽልማቱ ወይም እውቅናው የተሰጠበትን ጊዜ እና ምክንያት፤ ሽልማቱን የሰጠዉ ተቋም እና

ሌሎች ስለሽልማቱ ትክክለኛ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ የጤና ተቋሙን ስም፣ደረጃ፣ በደረጃው መሰረት የሚሰጠውን አገልግሎት፤ እና አገልግሎቱን የሚሰጥበትን አድራሻ መያዝ አለበት፡፡

6. <u>ስለ ሥነ-ምግባር</u>

ከጤና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያለው ማስታወቂያ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን ስነ-ምግባሮች ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆን አለበት፡-

1) የሌሎች ጤና ተቋማት አገልግሎትን እና የጤና ባለሙያዎችን ክብር ያለማንቋሸሽ፤
2) በጤና ተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ከሌሎች ባለሙያዎች የተሻሉና የተለየ የሙያ ብቃትና እውቀት ያላቸው በማስመሰል ከመግለጽ መቆጠብ፤
3) አገልግሎት ለመስጠት ልዩ የሆነ ንጥረ ነገር እንደሚጠቀም ወይም የተለየ ፈውስ የሚገኝበት ተቋም እንደሆነ በማስመሰል አለመግለጽ፡፡
4) ተገልጋዮች የጤና ተቋሙን አገልግሎት ካላገኙ በጤናቸው ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ የሚያሳይ አለመሆን፤
5) በዓለም አቀፍ እና ብሄራዊ ህጎች ጥበቃ የሚደረግላቸዉን እንደ ቀይ መስቀል፣ ቀይ ጨረቃ ወይም ቀይ ክሪስታል ስሞች፣ አርማዎች ወይም ምልክቶችን ወይም የሌሎች ቋማት ሎጎዎች ከሚመለከተዉ አካል ፍቃድ ሳይኖር በቀጥታ ወይም አሳሳች በሆነ መልኩ አለመጠቀም፤ እና
6) የተገልጋይን ክብርና ሥነ-ልቦና አለመንካት፡፡

7. <u>ስለ ምስክርነት</u>

1) ማንኛዉም የጤና አገልግሎት ማስታወቂያየሚያዘጋጅ ሰዉ ምስክር የሚያሳትፍ ከሆነ የሚሰጠዉ ምስክርነት የተሰጠዉን ህክምና የሚመለከት መሆን የለበትም፡፡
2) ከጤና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያለው ማስታወቂያ ላይ በምስክርነት የሚሳተፍ ግለሰብ ፈቃደኝነቱን በጽሁፍ የሰጠ እና አገልግሎቱን በትክክል ያገኘ ሰዉ መሆን አለበት፡፡
3) ከጤና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያለው ማስታወቂያላይ በምስክርነት የሚሳተፍ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወይም የአእምሮ ጤና ችግር ያለበት ወይም በራሱ መወሰን

የማይችል ሰዉ ከሆነ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ሞግዚት ወይም በህግ ስልጣን የተሰጠዉ ሰዉ የጽሁፍ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት
## የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ ስርጭት እና የአስተላላፊ ግዴታ

### 8. የአስተላላፊ ግዴታ

ማንኛውም የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ የሚያስተላልፍ ሰዉ ማስታወቂያዉ፡-

1) በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ግዴታዎችን ባሟላ መልኩ የተዘጋጀ ስለመሆኑ፤
2) የሚያሰራጨዉ ወይም የሚያስተላልፈዉ መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ ከሚመለከተዉ አካል የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

### 9. ወቅታዊነት

በማንኛዉም የጤና ተቋም ወይም አስተላላፊ የሚሰራጭ የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ፡-

1) ወቅቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፤ እና
2) ወቅታዊ የህብረተሰብ የጤና አደጋዎችንና ወረርሽኝ ቅድሚያ ተሰጥቶ ማሰራጨት

አለበት፡፡

### 10. ማሰራጫ መንገድ

1) የጤና አገልግሎት ማስታወቂያማሰራጫ መንገድ ይዘቱን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡
2) በመገናኛ ብዙሃን ከሚሰራጩ ማስታወቂያዎች በተጨማሪ እንደመኪና፣ ኮፊያ፣ ቲሸርት፣ ቢልቦርድ፣ ባነር፣ ፖስተር፣ብሮሸር፣መጽሄት፣ፎቶ፣ ስዕል፣ካርቱን እና መሰል ቁሳቁስ ላይ የሚተላለፉ የጤና አገልግሎት ማስታወቂያዎች ወይም መልዕክቶች በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡ የዝግጅት እና ስርጭት መስፈርቶችን ያሟሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ አስተዳደራዊ ቅጣት፤ ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት

### 11.አስተዳደራዊ ቅጣት

1) ማንኛዉም በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ (4)-(6) የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በመጣስ የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ያስተላለፈ ወይም በሌላ አካል እንዲተላለፍ ያደረገ የጤና ተቋም ከአስራ አምስት ሺህ እስከ ሀምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2) የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ ላይ ፍቃደኝነቱን በጽሁፍ ያልሰጠ ወይም አገልግሎቱን በትክክል ያላገኘ ሰዉን በምስክርነት ያሳተፈ የጤና ተቋም ከሀያ ሺህ እስከ ሀምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3) የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ ላይ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን ወይም የአእምሮ ጤና ችግር ያለበት ወይም በራሱ መወሰን የማይችል ሰዉን ከወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ሞግዚት ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጠዉ ሰዉ የጽሁፍ ፍቃድ ሳይሰጥ በምስርነት ያሳተፈ የጤና ተቋም ከሀምሳ ሺህ እስከ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4) ማንኛዉም አስተላላፊ በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 8 እስከ 10 የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የጤና አገልግሎት ማስታወቂያ ያስተላለፈ እንደሆነ ከአስር ሺህ እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) ድረስ ከተጠቀሱት ቅጣቶች ዉስጥ የተቀጣ የጤና ተቋም ቅጣቱን በ3 ወር ዉስጥ የማይከፍል ከሆነ ቅጣቱን እስኪከፍል ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ታግዶ የሚቆይ ይሆናል፡፡

### 12. ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሰረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ቅሬታ ያለዉ ሰዉ በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 በተቀመጠዉ ስርዓት መሰረት ወይም አግባብነት ባለዉ የክልል ህግ መሰረት የቅጣት ዉሳኔዉን ለሰጠዉ አግባብ ያለዉ አካል ቅሬታዉን ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. ህጋዊነት

ማንኛዉም የአንድ ጤና ተቋምን የጤና አገልግሎት ማስታወቅያ የሚያዘጋጅ ወይም የሚያሰራጭ ሰዉ ጤና ተቋሙ አግባብነት ካለው አካል የተሰጠ ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለዉ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

### 14. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1) የጤና ተቋም አገልግሎት ማስታወቂያ መመሪያ ቁጥር 387/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2) ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 15. መመሪያዉ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በጤና ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ሚያዝያ፣ 2018 ዓ.ም

ዶ/ር መቅደስ ዳባ
የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር

# Directive No. 1134/2026

## Directive on the Production and Dissemination of Health Service Advertisement

Whereas, unethical production and dissemination of health service advertisement is creating a baized attitude with in the community.

Whereas, it is necessary to create a system which enables producers and disseminators of health service advertisements to work in a way respecting ethics and culture of the community.

Whereas, to lead health service advertisements in transparent and accountable manner, it is important to issue directive which can implement the production and dissemination responsibilities of such works stated on the Health Service Administration and Regulation Proclamation no 1362/2024.

Now therefore, pursuant to Article 58 sub article 2 of Health Service advertisement and Regulation Proclamation No.1362/2024, Ministry of Health has issued this directive.

## Part one

## General provision

1. **Short title**

This directive may be cited as **" Directive on the Production and Dissemination of Health Service Advertisements No. 1134/2026."**

2. **Definition**

In this directive

1) **“Proclamation”** means Health Service Administration and regulation Proclamation No. 1362/2024.
2) **"Health Service Advertisement"** means an advertisement that relates with a health service and disseminated through advertisement dissemination medium to promote the name, logo, trademark, or objective of the health institution.
3) **"Advertiser"** means a person to whom a health services advertisement, its service, name, logo, symbol, objective, or similar information is disseminated through the media.
4) **"Disseminator"** means a person who disseminates health service advertisements, through dissemination medium, by providing airtime, print space, or other similar ways.
5) **"Dissemination Medium"** means Mass media, Outdoor advertising, Health education programs, Telecommunications-based text and voice messages, social media and websites, digital media or any other similar dissemination channels used for advertising health service Advertisement.
6) **“Mass Media”** has a definition stated under article 2(1) of media proclamation no 1238/2021
7) **"Appropriate Body"** means an institution that regulates health institutions or Ethiopian Media Authority, as the case may be.
8) **"Person"** means natural or juridical person.
9) Any expression in masculine gender includes feminine.
10) Any words and phrases defined in the Proclamation shall apply in this Directive.

3. **Scope of Application**

This Directive shall be applicable all over the country on health service advertisements s; and on a person who produces, advertises or disseminates such works.

# Part Two

## Production of Health Service Advertisements

4. **Language Usage**

The production of any Health service advertisements shall be: -

1) in a language that the audience speaks;
2) in a manner that considers the benefits and inclusivity of persons with disabilities;
3) clear or free from excessive professional jargons.

5. **Content**

1) When producing Health service advertisement the content shall:
   a) respect health policy, consider other health issues, and safeguard the health or safety of the community.
   b) consider the audience the message is transmitted for.
   c) keep the culture and values of the community.
   d) be free from words like `Prior choice`; `Everyone's choice` and other similar words.
   e) contain accurate information that demonstrates the health service is provided by the health institution.
   f) Contain the time and reason of the prize is awarded, the organization that awarded the prize and other accurate information about the awarded prize, if the health institution obtains regional or international prize for the service it grants and want to advertise about the prize or recognition.
2) Without prejudice to sub article 1 of this article, Health service advertisements shall contain the name and level of the health institution, the service provided according to its level, and the address at which the service is provided.

6. **Adherence to Ethics**

The production of Health Service Advertisements shall take in to consideration the following ethics: -

1) not to dishonor the service provided by other health institutions and the health professionals.
2) To refrain from expressing and pretending that the health professionals working in the health institution are superior and have distinct professional skills and knowledge.
3) Not to express as if the institution is using a special substance for providing the service or is a place of healing;
4) Not to describe that the clients face health damages if they don't get the service of the health institution.
5) Not to touch the honor and psychology of a client.

7. **Testimony**

1) Any person who produces health service Advertisements wants to participate a witness, the testimony given shall not be on the clinical treatment.
2) A person who participates as a witness on health service advertisements shall be the one who has given his consent in written and who has accurately received the service.
3) If the person who participates on health service advertisement is a minor; has mental health problem; or is unable to make decisions by himself; written consent of his parents, guardians, caregivers, or close relatives shall be obtained.

## Part Three

## Dissemination of Health Service Advertisements and Obligation of the Disseminator

8. **Responsibilities of the Disseminator**

Any person who disseminates health service advertisements shall ensure፡-

1) the advertisement, news report or artwork is prepared fulfilling the responsibilities stated on this directive;
2) from the concerning organ that the information disseminated is accurate.

9. **Up-to Date**

Any health service advertisement disseminated by a health institution or a disseminator shall: -

1) ensure if it is an updated;

2) disseminate by giving priority to public health risks and emergencies;

10. **Medium of Dissemination**

1) The medium of dissemination for health service advertisement shall take in to consideration its content.
2) In addition to advertisements disseminated through mass media, health service advertisements or messages disseminated on materials such as vehicles, capes, T-shirts, billboards, banners, posters, broachers, magazines, photo, pictures, cartoons and similar materials shall fulfill the production and dissemination criteria set forth in this directive.

## Part Four

## Administrative Measures; Complaint Submission and Grievance Handling

**11. Administrative Measures**

1) Any health institution that produces and disseminates or cause it to be disseminated by another party a health service advertisement that violates the provisions stated from sub article (4)-(6) of this directive the health or safety of the community, or that undermines the community's values and culture, shall be fined a penalty ranging from Fifteen Thousand to Fifty Thousand Birr.
2) Any health institution that participates a person who doesn't gave his written consent or who didn't get a service at the institution as a testimony shall be fined a penalty ranging from Twenty Thousand to Fifty Thousand Birr.
3) A health institution that participates a child who has not attained the age of maturity, a person with a mental health problem, or a person who cannot decide by himself, without written permission from the parent, guardian, caretaker, or someone legally authorized, shall be fined a penalty ranging from Fifty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

4) Any disseminator who transmits a health service advertisement violating the provisions stated from Articles 8 to 10 of this directive shall be fined a penalty ranging from Ten Thousand to Thirty Thousand Birr.
5) Any health institution that does not pay the penalty stated from sub article (1) up to (4) of this article that is imposed on it within 3 months, the certificate of competence shall be suspended until the penalty is paid.

**12. Complaint Submission and Grievance Handling**

Any person who has a complaint regarding an administrative penalty given as per article 11 of this directive may submit his complaint, based on the procedures set on the Federal Administrative Procedure proclamation no 1183/2020 or relevant Regional laws, to the appropriate body who has given the penalty.

## Part Five

## Miscellaneous Provisions

**13. Legality**

Any person who produces or disseminates the health service advertisement of the health institution shall confirm whether the health institution has a valid certificate of competency issued by the relevant body.

**14. Repealed and Inapplicable directive and practices**

1) Directive on Health Service advertisement no. 387/2013 is repealed by this directive.
2) Any directive or practice that contradicts this directive shall have no effect on matters covered herein.

**15. Effective Date of the Directive**

This directive shall be effective from the time it is publicized on the Ministry of Health's website, after registration at the Ministry of Justice.

**Done at Addis Ababa, Ethiopia**

**May, 2026**

**Dr. Mekdes Daba**

**Minister of Ministry of Health**